# PEOPLES ALLIANCE FOR FREEDOM AND DEMOCRACY (PAFD)

OFFICE OF PRESIDIUM

Date: August 20, 2016

Tel: +49-15145279816
+44-7940624477

Ref.:

Fax:


## ሁሉም የኢትዮጵያ የፖለቲካ ሃይሎች በሃገሪቷ የሽግግር ወቅት ስርዓትን እውን ለማድረግ ከህዝቦች ትብብር ለነጻነትና ለዲሞክራሲ ጋር እንዲሰሩ የቀረበ ጥሪ

የህዝቦች ትብብር ለነጻነትና ለዲሞክራሲ የኣምስት የፖለቲካ ድርጅቶች ትብብር ነው። የህዝቦች ትብብር ለነጻነትና ለዲሞክራሲ ኣባል ድርጅቶች የህዝቦቻቸውን ነጻነትና የዲሞክራሲ መብቶች እውን ለማድረግ ከ20 እስከ 40 ዓመታት ትግል ኣካሂደዋል። ከኢትዮጵያ ህዝብ ብዛት 67% የሚሆነውን የሚወክሉት እነዚህ ድርጅቶች ትግል ባካሄዱባቸው በነዚህ ዓመታት ድርጅታዊ ኣቅምና ብቃታቸውን እንዲሁም ያላቸውን ሃብት በማጎልበት ለነጻነትና ለዲሞክራሲ እያካሄዱት ያለውን ትግል በማፋፋም ላይ ይገኛሉ።

የህዝቦች ትብብር ለነጻነትና ለዲሞክራሲ ኣባላት በኢትዮጵያ ለነጻነትና ለዲሞክራሲ መታገል የሚያስችላቸውን መዋቅሮችና ኔትዎርኮች በህዝባቸው ውስጥ በተጠናከረ መልኩ ዘርግተዋል። የትብብሩ ኣባላት ትግልም የሚታገሉላቸውን ህዝቦች ተጨባጭ ሁኔታዎችና ፍላጎት ላይ በመመርኮዝ ጠንካራ መሰረት ይዞ እየተፋፋመ ነው።

የህዝቦች ትብብር ለነጻነትና ለዲሞክራሲ ኣባል ድርጅቶች በቅርቡ የትጥቅ ትግልና ህዝባዊ ንቅናቄ እያካሄዱ ባሉባቸው ኣካባቢዎች ትግላቸውን በማቀናጀት ላይ ይገኛሉ። በመሆኑም በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ሁሉም ህዝቦች ነጻነታቸውንና ዲሞክራሲያዊ መብቶቻቸውን እስከሚጎናጸፉ ድረስ በመላው ኢትዮጵያ ከተጠበቀው በላይ በከፍተኛ ፍጥነት እየተቀጣጠለ ያለው ህዝባዊ ንቅናቄ ኣይቆምም ብለን እናምናለን።

የህዝቦች ትብብር ለነጻነትና ለዲሞክራሲ ዓላማ፣ ህዝቦችን በማንቃትና በማደራጀት የትብብሩ ኣባል ድርጅቶችን የትግል እንቅስቃሴዎች፣ ሃብትና እውቀት ኣቀናጅቶ ኣምባገነኑን የሕወሃት ስርዓት ከስልጣን ማስወገድና በዲሞክራሲ መብቶችና የህዝቦች የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት ላይ የተመሰረተ የሽግግር ወቅትን እውን ማድረግ ያለመ ስርዓትን ማረጋገጥ ነው።

የህዝቦች ትብብር ለነጻነትና ለዲሞክራሲ እውነተኛና ሁሉን-ኣቀፍ የሆነ የፖለቲካ ስርዓትን በመመስረት በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚገኙ ሁሉም ብሄሮችና ብሄረሰቦች ጥያቄዎች ምላሽ የሚያስገኝ የሰብዓዊ መብት መከበርን እውን ለማድረግ ይሰራል። ከዚህም ሌላ በሃገሪቷ ብሄሮችና ብሄረሰቦች መካከል በተደጋጋሚ ለሚታዩ ኣለመግባባቶችና ግጭቶች ለኣንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ፍጻሜ ለማበጀት እየታየ ያለውን ፍላጎትና የሚደረገውን ጥረት ለማሳካት ይታገላል።

በኢትዮጵያ ለዓስርተ ዓመታት እየተካሄደ ያለው የትጥቅ ትግልና የቅርብ ጊዜው ህዝባዊ ኣመጽ ሃገሪቷን የከፋ ቀውስ ውስጥ መክተቱን ሁሉም ይገነዘባል። የኢትዮጵያ መንግስት በከፍተኛ ህዝባዊ ማዕበል ተውጦና ሃገሪቷን ማስተዳደር ተስኖት እየተንገዳገደ እንዳለ በገሃድ የሚታይ ሃቅ ነው።

በተለይም የኦሮሞ ህዝብ ላለፉት ዘጠኝ ወራት ሳያቋርጥ እያካሄደ ያለው ኣመጽና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በኣማራ ክልል እየተካሄደ ያለው ተቃውሞ እንዲሁም ሌሎችም የሃገሪቷ ብሄሮችና ብሄረሰቦች ለዲሞክራሲና ለነጻነት እያካሄዱት ያለው እንቅስቃሴ የሕወሃት ስርዓትን ፍጻሜ እያቃረበ ነው። ስርዓቱ በሃገሪቷ ህገ-መንግስትና በኣለም-ኣቀፋዊና ክልላዊ ህጎች መሰረት ህዝቦችን ማስተዳደር ባለመቻሉ ሰላማዊ ዜጎችን በዘግናኝ ሁኔታ በጅምላ መግደልን እንደመፍትሄ በመውሰድ ሁኔታውን ይበልጥ እያወሳሰበ ይገኛል።

የህዝቦች ትብብር ለነጻነትና ለዲሞክራሲ የኣሁኑን ወቅታዊ ሁኔታ በጥልቀት በማየት በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ሁሉም ብሄሮችና ብሄረሰቦች ከትብብሩ ጎን በመሰለፍ እየተካሄደ ያለውን ፍልሚያ ከግቡ ለማድረስ እንዲሰሩ ጥሪ ያቀርባል። ተጨቋኝ ህዝቦችና ተራማጅ ሃይሎች ከውድቀት ኣፋፍ ላለው የወያኔ ስርዓት ፍጻሜ በማበጀት፣ የሁሉም ኣካላት ተሳትፎ እውን የሆነበት የሽግግር ስርዓትን ለማሳካት ከትብብሩ ጎን ተሰልፈው እንዲሰሩ መልዕክታችንን እናስተላልፋለን። መላው የሃገሪቷ ህዝቦችና የፖለቲካ ሃይሎች ከኣሁኑ የበለጠ ተጨባጭ እርምጃ የሚወሰድበት ጊዜ እንደሌለ ተገንዝበው ከትብብሩ ጋር በመስራት የሽግግር ስርዓትን ለማስገኘት ተጨባጭ ኣዎንታዊ እርምጃ እንዲወስዱና ገንቢ ሚና እንዲያበረክቱ እንጠይቃለን።

የህዝቦች ትብብር ለነጻነትና ለዲሞክራሲ በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ህዝቦች ውክልና የተረጋገጠበትና ህዝቦች መጻዒ እድላቸውን ሊወስኑ የሚችሉበትን የሽግግር መንግስት እውን ለማድረግ ይሰራል። ስለሆነም እውነተኛ ለውጥ ለማስገኘት የሚሰሩ ሃይሎችና ቡድኖች እንዲሁም ህዝቦቻችንን እንወክላለን የሚሉ ኣካላት ሁሉ ወደ ህዝቦች ትብብር ለነጻነትና ለዲሞክራሲ በመቀላቀልና ለትብብሩ ጥሪ ኣፋጣኝ ምላሽ በመስጠት የሽግግር መንግስት ስርዓትን እውን ወደ ማድረጉ የሚያመራ የሽግግር ኮንፈረንስ ለማቀናጀት እራሳችንን እንድናዘጋጅ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን። ይህም በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙትን ሁሉንም ህዝቦች የሚፈይድና ህዝቦች ለሚመኙት እውነተኛ ሰላም፣ ዲሞክራሲና የሰብዓዊ መብቶች መረጋገጥ እንደድልድይ ያገለግላል ብለን እናምናለን።

**ዲሞክራሲና ነጻነት ለሁሉም!**

**የህዝቦች ትብብር ለነጻነትና ለዲሞክራሲ የፕሬዚዲዬም ጽህፈት ቤት**
**ነሃሴ 20, 2016ዓም**